የረቡዕ የካቲት 1 1998 ዓም ( የፌብርዋሪ 8 2006)

## የፍኖተ ዴሞክራሲ ሐተታ

## ብሔራዊ አቅጣጫችን ወዴት ነው?

ከአስራ ዘጠኝ መቶ ስድሳ ስድስት ዓመተ-ምህረት ጀምሮ÷ ሀገራችን ኢትዮጵያ በታሪኳ አጋጥሟት በማያወቅ ከፍተኛ የለውጥ ማዕበልና ቀውስ ውስጥ እንደቆየችና አሁንም በዚሁ ሁኔታ እንደምትገኝ ከጨቋኝ ገዢዎቿና ጠላቶቿ በስተቀር ማንም የሚክደው ሀቅ አይደለም:: ከስድሳ ስድስት ዓመተ ምህረት ወዲህ አያሌ ሀገሮች ብሔራዊ -ሕዝባዊ አመፅ አድርገዋል:: በሂደቱም፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ የከፈለውን ያህል እንኳ ባይሆን÷ ከባድ መስዋዕት ከፍለዋል:: ግን ከሞላ ጎደል ዓላማቸውን መትተዋል ማለት የሚቻል ይመስለናል:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ዐብዮት ከተጀመረ ወዲህ ÷ አያሌ ሀገሮች የየራሳቸውን ብሔራዊ ዐብዮት ማድረጋቸው የኅብረተስብ ዕደገትና ሂደት ክስተት በመሆኑ÷ ሊያስገርም ባይችልም÷ ያመፁን ፍሬና ውጤት አግኝተው ወደ ብሔራዊ ዕድገትና የልማት እንቅስቃሴ ሲያመሩ÷ እኛ ግን የዚህ ዕድል ተቋዳሾች ባለመሆናችን÷ ከመገረም አልፈን እያዘንን እንገኛለን:: ከእኛ በኋላ÷ ኒካራጓ÷ ደቡብ አፍሪካ÷ ኢራቅ÷ እንዲሁም በርካታ የደቡብ አሜሪካ ሀገሮችና ሌሎቹም በዓለም ዙሪያ የሚኖሩ ሕዝቦች በአደረጉት ሕዝባዊ አመፅ÷ ከፍተኛ ለውጥ አድርገው የሚፈልጉትን የዕድገት ዕመርታ አስመዝግበዋል:: እኛ ግን በታሪካችን አግኝተነው የማናውቀው÷ እጅግ በጣም ከባድና ረዥም መከራ ቢገጥመንም፤ ጎልቆ መሳፍርት ዜጋ ብንገብርም÷ አህዙ በትክክል የማይታወቅ ምሁርና ወጣት እንደቅጠል ቢረግፍም÷ አሁንም÷ ልማቱና ዕድገቱ ቀርቶብን÷ ሠላምና መረጋጋት እንኳን አላገኘንም::

<u>ሦስተኛውን አምባገነን ሥርዓት ጥለን÷ ሌላ አራተኛ ጨቋኝ መንግሥት እንዳይመጣብን የምንሰጋው ዜጎች ቁጥራችን ቀላል አይደለም ብለው የሚያምኑ አሉ</u>:: በዚህ አሁን በተያዘው ሁኔታና ሂደት÷ ከሕዝብ ፍጅትና ዕልቂት÷ ከሀገር ጥፋትና ውድመት ለመከላከል የሚያስችለን ሁሉንም የሚያካትት መሠረተ-ሰፊ÷ አቅጣጫ ሰጭና ሁሉንም የሚመራ ብሔራዊ የጋራ መድረክ አላገኘንም :: ከዕስራትና ስደት÷ ከረሀብና ጠኔ÷ ከጅምላ ጭፍጨፋና ግድያ÷ ከጦርነትና ከፍጅት÷ ነፃ አልወጣንም:: አሁንም ዋይታና ለቅሶ÷ ስቆቃና ሀዘን የብሔራዊ መታዋቂያችንና የማንነታችን መለያ እንደሆነ ነው:: የዓለም ተመጽዋቾች÷ የጎረቤቶቻችን መሳለቂያዎች÷ የአምባገነኖች ጭቆና ሰለባዎች ከመሆን አልዳንም:: ከዚህ ሁሉ ምፅዓተ- ፍዳ ÷ዘመነ-ፍዳ ለመውጣት አልቻልንም:: ይህንን ሁሉ ማውሳታችን÷አሁን ከገባንበት ሁኔታ ለመውጣት የሚያስችለንን ብልህት እንድንገናብ እንጅ÷ የጨለምተኝነት አባዜ ይዞን አይደለም::

ዕውነቱን ተናግረን ከመሸበት እንደር ካልን ግን፥ አሁንም፥ለብሔራዊ ችግራችን ማስወገጃ የሚሆነን ብሔራዊ መፍትሄ ለመፈለግ የሚያስችለንን ብሔራዊ አቅጣጫ ለመቀየስ ቀርቶ፥ የጋራ ብሔራዊ የትግል አጀንዳ መቅረፅ እንኳን ተስኖናል፡፡ እስካሁን! ሌላው ቀርቶ፥ ምን ዓይነት ብሔራዊ ዕፀፅ እንደገጠምን እንኳ ደፍረን ለመነጋገር ዕወቀቱም፥ ትዕግስቱም ሆነ ትህትናው፥ ቆራጥነቱም ሆነ ግልፅነቱ የለንም፡፡ ሀቀኝነት፥ ታማኝነት፥ ተማምኖ፥ ለመከባበር፥ ተዋውቆ ለመተባበር፥ ከአድማስ ባሻገር ለማየት፥ስለ ብሔራዊ ራዕይ ለማሰብ፥ ከግል ሰብዕና፥ ከከንቱ ውዳሴና ከራስ ድርጅት ጥቅም በላይ ለመመልከት ገና ብዙ ምዕራፍ መሄድ እንዳለብን የተገነዘብነው አንመስልም፡፡ ዘለዓለም ስለ ችግራችንና ድክመታችን፥ እያወራን መኖሩ፥ እስካሁን ምንም መፍትሔ እንዳላስገኘልን ከልብ ተቀብለን፥ በመፍትሔ ፍለጋው ላይ ማተኮር ይገባናል፡፡ የሀገራችንን ሁለንተናዊ ችግሮች ለመፍታት የሚያስችለንን ብልኃትና ዘዴ ማግኘት አጣዳፊ ተግባራችን እንጅ፥ በስብሰባ ብቻ የሚገለፅ ነባቢት ሆኖ የሚቀር ጉዳይ አይደለም፡፡ በታሪክ ሂደት ውስጥ የሚፈራረቅ ትውልድ፥ የራሱን ብሔራዊ ችግር ፈትቶ ለሀገርና ለወገን የሚጠቅም ሥራ ሰርቶ ያልፋል እንጅ፥ የራሱን ችግር ለተተኪው ትውልድ አውርሶ አይሄድም፡፡ ቀደምት አባቶችና እናቶችም አድርገውት ያለፉት ይህንኑ ነው፡፡ ብሔራዊ አቅጣጫ፥ ቀይሶ በብሔራዊ ሂደት መጓዝ ከተቻለ፥ በአስተማማኝ ሁኔታ ከብሔራዊ ግብ መድረስ ከባድ አይሆንም፡፡ የጋራ አጀንዳን ነድፎ፥ የጋራ ብሔራዊ ዓላማን አንግቦ፥ ብሔራዊ ግብን ለመምታት ያነጣጠረ ትግል፥ በአቸናፊነት እንደሚጠናቀቅ በርካታ የታሪክ ማስረጃዎች መጥቀስ የሚቻል ይመስለናል፡፡

ታዲያ ይህን ሀቅ መቀበልን ከቻልን፥ ለምን ብሔራዊ አቅጣጫው ጠፋብን? ይህንን መሠረታዊ ጥያቄ በተገቢ መልኩ መልሰን፥ አቅጣጫችንን እንዳንቀይስ ከሚያደርጉን ብዙ እንቅፋቶች አንዱ፥ከራሳችን ጋር ታርቀን ከሌሎቹ ጋር ለመታረቅ ፈቃደኞችና ዝግጁዎች አለመሆናችን ይመስለናል፡፡ ታዲያ ይህ ደግሞ በበኩሉ፥ ጠላቶቻችን፥ " ሀበሾች፥ እንኳን ተስማምተው በጋራ ሊሰሩ ቀርቶ፥ ላለመስማማትም ቢሆን የሚስማሙ አይደሉም" የሚለውን ፥ " ጠላት ይቀባል ጥላት" ዝባንዝንኪ ተረት ተረት ማጠየቂየ እንደመስጠት ይሆናል፡፡ ይህን የሚቀበሉ ካሉ ተሳስተዋል፡፡ እኛ በበኩላችን ግን፡-

- የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘመናት በጋራ ተስማምቶ ተባብሮ ሀገሩን በነፃነት ጠብቆ ማቆየቱን፥

- ገዥዎች ከሚያመጡት የየግላቸው ጦርነትና ውጊያ በስተቀር፥ ኢትዮጵያውያን በብሔርም ይሁን በጎሳ፥ በዘርም ይሁን በቋንቋ፥ በኃይማኖትም ይሁን በክልል የተጋጩበት አጋጣሚ ታሪክ መመዝገቡን አለማወቃችንን፡-

- ሴቶች በጥጥ ደቦ፥ ወንዶች በእርሻ ወበራ፥ በማኅበራዊ፥ ኢኮኖሚዊ፥ ባኅላዊና ኃይማኖታዊ ትስስር አብረው የኖሩ መሆናቸውንና

- የጋራ ችግራቸውን በጋራ የመፍታት ልምዳቸውን ነው የምናውቀው።

ይህ የሕዝብ ፤ ታሪካዊ፥ ማኅበረሰባዊ፥ ባኅላዊና ኢኮኖሚያዊ ትስስር ደግሞ በበኩሉ፥ ብሔራዊ አቅጣጫንና ራዕይን በማገናዘብ አብሮ ተስማምቶና ተከባብሮ ለመኖር የሚያስችላቸው ኢትዮጵያዊ ዓብነትና ምሥጥራቸው ነበር። ይህንን ሀገራዊ ዓብነት፥ መሠረት አድርገን፥ ዛሬ እኛ፥ የጋራ ብሔራዊ አጀንዳን ነድፈን፥ ሀገራዊ ራዕያችንን አማትረን፥ የትግል አቅጣጫችንን ቀይሰን በመታገል፥ ወያኔን ከሥልጣን የማናወርደበት አንዳችም ምክንያትና እንቅፋት ይኖራል ብለን አናምንም።

"ሁሉም መንገዶች ወደ ሮማ ያመራሉ" እንደሚባለው፥ እኛም፥ ሁለንተናዊ አቅማችን፥ ትኩረታችን፥ ኃይላችን፥ አዕምሯችንና ዓላማችን ወደ አንድ ብሔራዊ አቅጣጫ እንዲያመሩ ማድረግ፥ የወቅቱ መፈከርና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነተኛና ብሔራዊ ጥያቄ ሆኗል። ይህንን አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄ በመሠረተዊ ሂደቱ መመለስ ከተቻለ ደግሞ፥ ብሔራዊ አቅጣጫን የቀየሰ ትግል፥ ምን ዓይነት ስልትና ስትራተጂ ማቀፍ አለበት? የሚለውን ዓበይት ጉዳይ ማናሳት ሊኖርብን ነው።

በእኛ ዕምነት፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የማነኛውም ጉዳይ ሁሉ ባለቤትና አዛዥ፥ አድራጊ-ፈጣሪ፥ ወሳኝና ፈራጅ ነው እንላለን። ሁሉ በእጁ-በደጁ በመሆኑም፥ የህግ የበላይነትንም ይሁን የራሱንና የሀገሩን ሉዓላዊነት አስከብሮና ጠብቆ ፥ በነፃነትና በደስታ መኖር የሚችል ሕዝብ ነው ብለን እናምናለን። የሰላም ጌታ፥ የጦርነትም አሰወጋጅ በመሆኑ፥ መለስና ተባባሪዎች የሠላሙን በር ሁሉ ቢዘጉበትም፥የሰላም ባለቤት በመሆኑ፥ ጦርነትና ጥፋት፥ እልቂትና የሀገር ውድመት እንዳይመጣ የመከላከል ኃይልና ጉልበት እንዳለውም እነገነዘባለን። ይህ ኃላፊነት የጎደለው ጠባብ ብሔረተኛ፤አሸባሪና አጥፊ የመለስ ዜናዊ ቡድን፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ እርስ በእርሱ እንዲተላለቅ ወደ ጦርነት አፋፍ እየገፋው መሆኑ ግልፅ ቢሆንም፥ ሕዝባችን ግን፥ አሁንም ቢሆን ከእርስ በርስ ጦርነት ይልቅ፥ የሰላም ዋጋና ጥቅም እጅግ የከበረና ውድ መሆኑን ከልብ ያምናል። ይህ ዕምነቱ ከፍርኃትና ከድክመት የመነጫ ሳይሆን፤ የወያኔን የአጥፎቶ መጥፋትን ተልዕኮ በሚገባ ስለተረዳው ነው። በወያኔ ወጥመድ ላለመግበት የሚደረገው ቻይነትና ወደ እርስ በርስ መተላለቅ አልገባም ብሎ እስከ መጨረሻው መቋቋም፥ የታላቅነትና የአቸናፊነት ምልክት እንጂ፥ የድክመትና የተሸናፊነት በጎርይ አይደለም። ታዲያ በአሁኑ ወቅት አቅጣጫችንና የትግል ስልታችንም ሆነ መሠረታዊና ዘላቂ ዕቅዳችን ምን መሆን ይገባዋል? ብለን ስናማትር፥ የሚከተሉትን ግንዛቤዎች በግምት ውስጥ ለማስገባት እንገደዳለን።

1) ምንም እንኳን በአሁኑ ወቅት፥ ወያኔ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሰላምና ህጋዊ ትግል በር ለመከርቸም ቢሻም፥ አሁንም ቢሆን፥ የኢትዮጵያ ሕዝብ የሰላሙን ትግል ወደ አርዕድ አንቀጥቅጥ ኃይል ለመለወጥ የሚያስችል ዕምቅ ኃይል አለኝ ብሎ ያምናል ብለን እናስባለን፡፡ይህ ከሆነ ዘንዳ ደግሞ፥ የሰላሙንና የዲፕሎማሲውን ትግል በበለጠ አቀናጅቶና አስተባብሮ መቀጠል የሚያስፈልግ ይመስላል፡፡

2) ወያኔን ለማንበርከክ ግን የሰላሙ ትግል ብቻውን ውጤት እንደማያመጣ ያለፉት 15 ዓመታት ተመክሮዎች ህያው ምስክሮች ሆነዋል፡፡ የሰላሙን ትግል የሚያጎለብት ተደጋጋፊና ጫና የሚያመጣ  ክንድና ጥርስ ማስፈለጉን ሁሉም አምኖበታል፡፡

3) በአንድና ሁለት ተራ ቁጥሮች የተጠቀሱትን ግንዛቢዎች አቀነባብሮ ተግባራዊ ለማድረግና ውጤት ለማስመዝገብ ከተፈለገ፥ በብሔራዊ ደረጃ ሀገርን ማዳን የሚያስችል፥ ሁሉንም ያካተተ ሀገራዊ ማዕከል መፍጠሩ አስፈላጊ ባቻ ሳይሆን ወሳኝም ጭምር ነው፡፡ ከዚህ ማዕከል ሊመነጭ የሚችለው ደግሞ፥ ብሔራዊ አቅጣጫ ቀያሽ የትግል ስልትና የዕቅድ ወይም ትልም አድማስ ይሆናል፡፡ ሁሉን ያካተተ ትግል ለማካሄድ በግድ አቅጣጫ ቀያሽ ማዕከል ማስፈለጉ /መፈለጉ ይዋል ይደር የሚባልበት ጉዳይ አይደለም፡፡ አቅጣጫ ካለ ደግሞ ታጋዩም ኃይል ይሁን ደጋፊው የሚሠራውን ሁሉ በሚገባ አውቆ ሁሉም የየድርሻውን ለማበርከት ይመቻዋል፡፡ አሁን አቅጣጫ አጥቶ በዳበሳና በመላ- ምት፥ የሚከላወተው ትግል፥ በአስቸኳይና ባልተጠበቀ ፍጥነት ግቡን ከመምታት የሚያቆመው ኃይል አይኖርም፡፡

በጋራ ለመታገል የጋራ ግብር ኃይል መስርቶና ግብን ተልሞ መገኘት ቀነ ቀጠሮ የሚሰጠው ግዳጅ አይደለም፡፡